# የብልጽግና ፓርቲ ከፍተኛ ሃላፊ የብልጽግና ፓርቲ
# ጸረ ሕገ መንግስትና ጸረ ህብረ ብሄራዊ ፌደራሊዝም መሆኑን አጋለጡ



ዓለም እንደሚያውቀው ሕገ መንግስት ምን ዓይነት መንግስት መመስረት እንዳለበት፣ የመንግስት መዋቅር ምን መሆን እንደሚገባውና እያንዳንዱ መዋቅር የሚኖረው ስልጣንና መዋቅሮቹ እርስ በርሳቸውና ከህዝብ ጋር የሚኖራቸው ዝምድና ምን መሆን እንዳለበት የሚደነግግ ፣ የዜጎችን መብት የሚዘረዝር፣ መንግስት የሚከታላቸው አቅጣጫዎችን የሚያብራራና የመንግስትን ስልጣን የሚገድብ ህጋዊና ፖለቲካዊ ሰነድ ነው። ይህ ሰነድ በዘመናዊ ማህበረ ሰብ ዜጎች ተስማምተው የሚያጸድቁት በህዝቦች መካከል የሚደረግ ማህበራዊ ስምምነት ነው። ይህ ሰነድ በአገሪቱ ውስጥ ካሉ ህጎች ሁሉ የበላይ ህግ ነው። በአንድ አገር ውስጥ የተረጋጋና አስተማማኝ ስርአት ሊኖር የሚችለው ሁሉም ህዝብ የአገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናትም ጭምር በሕገ መንግስት ብቻ መመራት ሲችሉ ነው። ሕገ መንግስት መንግስትና ህዝብ ስለ ሕገ መንግስቱ በቂ እውቀትና እምነት ጨብጠው ተግባር ላይ ሲያውሉት ብቻ ነው የማህበረሰብ የተረጋጋና ቀጣይነት ያለው እድገት የሚመዘገበው። ሕገ መንግስት በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን ህዝቦችንና የሁሉም የመንግስት ባለስልጣናት ተግባሮችን ስለሚገዛ ሁሉም በዚሁ እንዲተዳደሩ ያስገድዳል። ማንኛውም የመንግስት አካል ይህን የሚጻረር ህግ ማውጣትም ሆነ ተጻራሪ ተግባራትን መፈጸምን አጥብቆ ይኮንናል። ሕገ መንግስት ጠቅለል ያሉ መሰረታዊ መመርያዎችን ያቀፈና ለብዙ ዘመናት እንዲያገለግል ታስቦ ነው የሚጻፈው። ነገር ግን ለአዲሱ ዘመን የእድገት ደረጃ ሊመጥን ካልቻለ መጽሃፍ ቅዱስ ወይንም ቁርአን አይደለምና ሕገ መንግስቱ በሚደነግገው መሰረት ሊተረጎም፣ሊሻሻልና ዘመን ተሻጋሪ እንዲሆን ይደረጋል። እስከዛ ድረስ ግን የመንግስት አካላትና መላው ህዝብ በጥብቅ ሊከተሉት የግድ ይላል።

የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች የደነገገ፣ ኢትዮጵያ የተለያዩ ቋንቋዎች፣ባህሎችና ታሪኮች ባለቤት የሆኑ ኢትዮጵያውያን አገር እንደሆነች በጉልህ የተቀበለና እነዚህ ህዝቦችን የሚያስተዳድር ሌላ ህዝብ ሳያስፈልግ ራሳቸው የስልጣናቸው ባለቤት እንደሆኑ ደንግጎ የህዝቦች ባህል ቋንቋና የህዝቦች አሰፋፈር መሰረት ያደረገ የክልሎች አደረጃጀትን

ተቀብሎ ፌደራላዊ መንግስትን መስርቷል። እነዚህ ብሄር ብሄረሰቦች ወደ አንድነት የሚመጡት በሙሉ ፈቃዳቸው እንደሆነ እምነት ለማስጨበጥ ባልፈለጉበት ወቅትም የራስን እድል በራስ የመወሰን መብታቸውን ተጠቅመው ከህብረቱ መውጣት እንደሚችሉ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል በሚል መተማመኛ አንቀጾችን አስፍሯል። ይህ በመፈቃቀድ አንድ ማህበረ ኤኮናምያዊ ስርዓትን ለመመስረት አልሞ የጸደቀ ሕገ መንግስት **የአንድ ብሄር የበላይነትን በፍጹም አይቀበልም።** ይህ ህገ መንግስት እነዚህ ብሄር ብሄረሰቦች አንድነታቸውና ማንነታቸው ለዓለም የሚገልጹበት መለያ የሆነ ምልክት ከማሃሉ ያለው ባንዴራ በአንቀጽ 3 ደንግጓል። በተጨማሪ ደግሞ አዋጅ ቁጥር 48/1999 በዝርዝር ባንዴራው እስከነ ምስሉ አስፍሯል።

የብልጽግና ፓርቲ ከተመሰረተ በኋላ ብሄር ብሄረሰቦች ዶ/ር አብይ ከነዶክተር ብርሃኑ ነጋና መሳይ የብሄር ብሄረሰቦችን መብት ከማይቀበሉ ጽንፈኞች ጋር ብድብቅ እያሴረ ህብረ ብሄራዊ ፌደራሊዝማችንን በትኖ አሃዱአዊነትን ሊያነግስ፣ ህልውናችን፣ ባህላችንና ቋንቋችንን ሊያከስም የተነሳ ሴራ ነው የሚል ከፍተኛ ተቃውሞዎችን በማስነሳታቸው ከጠቅላይ ሚንስትሩ ዶ/ር አብይ አህመድ ጀምሮ የተለያዩ የፓርቲው ከፍተኛ ባለስልጣናት የብልጽግና ፓርቲ ያለውን ሕገ መንግስት የሚቀበልና ህብረ ብሄራዊ ፌደራላዊ ስርአቱን የሚያስቀጥል ነው፣ የብሄር ብሄረሰቦች መብቶችን አይደፈጥጥም እያሉ ደጋግመው ምለው ተገዝቷል።

በተግባር የሚታየው ግን ሌላ እየሆነ ነው። ትንሽ ሳይቆዩ ትላንትና ባህር ዳር የተደረገውን ህገ መንግስቱን የመጣስ ተግባር የብልጽግና ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች በሰሜን አሜሪካ የተለያዩ ግዛቶች እየተዘዋወሩ በግላጭ ሕገ መንግስቱን የመጣስ ዘመቻ እየደገሙት ነው። ብሄር ብሄረሰቦች ያጸደቁትን ባንዴራ በመተው የድሮ ልሙጡን ባንዴራ በረኸሙ ሰቅለው ተገኝቷል። ለአብነት ይሆናችሁ ዘንድ ዘ ሃበሻ ካሰራጨው ዜና ትመለከቱ ዘንድ ሊንኩን ከስር አስቀምጨላችሁ አለሁ።
https://youtu.be/buOv_qnGMv0

የአማራ ክልል ባንዴራ ነው እንዳንለው የአማራ ክልል ባንዴራ ነው ተብሎ ብህግ የጸደቀው ባንዴራ ከስር ያለው ነው።



ታድያ በሕገ መንግስቱ ያልጸደቀውን ልሙጡን ባንዴራ በረኸሙ ሰቅሎ መገኘት ሕገ መንግስቱን መጣስ አይደለምን? ይህ ህገ መንግስቱን የመጣ ምልክት ቀላል ኣይደለም። የብልጽግና ፓርቲ ጉዞና ለህገ መንግስቱ ታማኝ አለመሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። እነዚህ ሰዎች ዛሬ እንዲህ ካደረጉ ብሄርና ብሄረሰብ የሚል ቋንቋ እንደ እሬት ይመራቸዋልና ነገ በኢትዮጵያ ያለውን የክልሎች አከላለ አፍርሰው ኢትዮጵያን በአራት፣ ወይም እንደ ድሮ በጂኦግራፊ በከፍለ ሃገር እንደማይከልሉትና የብሄርና ብሄረሰብ ህልውናን እንደማያከስሙ ምን ዋስትና አለን?

የብሄር ብሄረሰብ መብቶችንንና ህገ መንግስታቸውን አከብራለሁ ያለ ፓርቲ ባንዴራቸውን ካላከበረ ምን ሊያከብር ነው？ለህገ መንግስቱ ያለው ታማኝነትስ እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል？ሽፍጥ ብዙ ርቀት መጓዝ አይችልም።

**ሃቀኛ ገጽታ መደበቅ አይቻልም። የብልጽግና ፓርቲ ከፍተኛ ሃላፊዎች የብልጽግና ፓርቲ ጸረ ሕገ መንግስትና ጸረ ህብረ ብሄራዊ ፌደራሊዝም መሆኑን በህገ መንግስት የጸደቀውን ባንዴራ አስወግደው ልሙጡን ባንዴራ በማንበልበል ገሃዱን ለዓለም አጋልጧል።**

**ኢትዮጵያ ሽመልስ**